# ሰሞንኛው ጉዳይ ላይ –

# ለትግሉ ቅድሚያ በመስጠት

**ዳዊት ዳባ**

**January 2, 2017**

የከፋ መሰዋትነት እየተከፈለበት ያለ ትግልውጤታማ ይሆን ዘንድ ሁላችንም ሊያስጨንቀን የሚገባ ነው፤ መሉ ጭንቅላታችንየተባበረአቅማችን ትግሉ ላይመዋል አለበት። ድርጊታችንምንግግራችንም ሆነሀሳባችን ሁሉ ትግሉን አሸናፊ ከማድረስ አኳያ የተሰላ መሆኑ ላይ እርግጠኛ መሆን አለብን።እንደዚህ መሆን እስካልቻልን የባርነት ዘመን ይቀጥላል። በትግሉ ሂደት የበዛ ሀላፊነትን የተሸከማችሁ ወገኖችትግሉ እዚህ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ አገዛዙ በሚወስዳቸው በየትኛውም አይነት እርምጃ ሊገታ አይችልም። አንድና አንድ የትግሉ ከግብ መድረስም ሆነ መንቀራፈፍ የሚወሰነው ለለውጥ በቆመው አካል አያያዝ ብቻ ነው።ሀላፊነትና የበዛ ድርሻ ያለን ክፍሎችስኬት ወይም ብቃት የሚለካው በቀጥታ ትግሉን አሸናፊ ማድረግ ከመቻል ጋር ነው። ይህን አይነቱን ታሪካዊ እድል በተለያየ ጊዜ አግኝተው ሳያውቁበት ቀርተው መሰዋትነት የተከፈለበትን ትግል አሸናፊ ማድርግ ያልቻሉት የበዙት ወድቀው እስከጭራሹ አልተነሱም ። መነሳት ከተባለ ተነሳን ያሉትም አሁን ያሉበት ደረጃ ለመድረስ ብዙ ዋጋ አስከፍሏቸዋል።የትኛውም አይነት ሰበብና ትንታኔ በኋላ ፋይዳ አይኖረውም።

መሰራት ያለባቸውን ስራዎች ዜጋውየድርሻውን ማድረግ በሚፈልግበት አሁን አስተባብሮማሰራት ላይ መካን። ፈጣን አመራርና አቅጣጫ ማስያዝ፤ በወረቀት ላይ በተቀመጠ እቅድ መንቀሳቀስ፤ ማስተባበርናትግሉንማቀናጀት። ቅራኔዎችን ማለዘብ ስህተቶችን በቶሎ ማረም የአሸናፊነት ሚስጥር ነው። አገዛዙ የሚወስዷቸውን እርምጃዎች በተመለከተፍጅት፤ ጅምላ እስር፤ ወታደራዊ ቀጠና፤ ኮማንዶ ፖስት፤ ጥገናዊ ለውጥ፤ ካብኔ ማዘበራረቅ የመዳከምና ፍፃሜውን የሚያሳዩ ሂደቶችም ናቸው። ለለውጥ እያታገለ ያለውን ክፍል በተመለከተ ግን ከትላልቅና ወሳኝ ጉዳዮች ተነስተንብናይው ለአገር ሉአላዊነት ሲባል፤የብሄር ብሄረሰቦችን መብት ለማስከበር ሲባል፤ ወደ አላስፈላጊ የርስ በርስ ግጭት ውስጥ እናዳንገባናታላለቅ የመብት ጥያቄዎችና የተለያዩ የመህበረሰቡ ከፍሎች ፍላጎቶች የመሳሰሉአገራዊ ቁም ነገሮችን ዛሬ ላይ ከትግሉ ፊት አብዝቶ ማሮጥ ውጤቱ ውድቀት ነው። ሲጀመር አብረውን የከረሙ መፍትሄ ልንሰራላቸው የሚገቡ ቁምነገሮችነበሩ። ማለፊያ የሆነ መፍትሄና በሰከነ ሁኔታ ሊያሻግረን የሚችለው ብለሀት ላይ ተጮሆበታል። ዛሬ ላይ ችግሩን ሲናገሩ እንደመስማት የሚያስጠላ ነገር የለም። መፍቴሄ መስራት የሚገባቸው ወገኖች ችግሩን ሲናገሩ እንደመስማት የሚያናድድም ነገር የለም። ውጤቱ ዜሮ ድምር በሆነ የፖለቲካ ጭቅጭቅ ምክንያት ተባብረን መታገል አቅቶን የህዘብ ትግል ሲጎዳና የጭቆና ዘምን ቀጥሎ እንደማየትም የሚያሳዝን ነገር የለም። በዋናነት መፍትሄ የሌለው የማይታለፍ ችግርም አይደለም። ስለወዘፍነው ዋዜማ ላይ ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ ያለን በመሆኑያልተለመደና ወሰብሰብ ያለ መንገድን አሸቷል።

1.ወሳኝ በሆኑ ክፍሎችና ዜጎች በተዘጋ በር፤ ከህዘብ ጀርባ፤ ከኔ ጀርባ፤ በጠረቤዛ ዙሪያ የሚሰራ እንጂ ባደባባይ ውይይት ሊሰራ አይችልም። ለዚህ ጊዜውም ቅንጦቱም የለም። በተደራጀ መንገድ ትግሉ ላይ ሊያበረክት የሚቸለውን አስተዋፃ አንድ ሁለት ብሎ ማስመዝገብየቻለ ሁሉ እስከተካተተና የሚያሻግሩን ገለልተኞች ወይ ሁሉ ባይገባበትም በአመለካካት ደረጃ ሁሉ እስከተወከለ

በቂ ነው።ውጪ ቀርቶ ጎታች አይኑር እንጂ ህዘብ በጭራሽ አይገደውም።ለዚህ ሁሌም ማናቸውንምተባብሮ የመታገል ሙከራዎችን ሲያሞግስና ስያበረታታ ነው በተደጋጋሚ የታየው።

2.አንድና አንድ ሰላማዊ ሽግግርን ስለመስራትና ትግሉን ስለማስተባበር እንጂ ላሉ የማያጣጣሙ ፍላጎቶች በሙሉ አንድ ሲደመር አንድ አይነት መፍትሄ የላቸውም። ይቁረጥ። ቢኖራቸውም ሁለት ብሎ ማስቀመጡ አሁን ትክክል አይደለም። ለመወሰን ህዘባዊ ውክልና ያለው ወገን የለምና። ጥያቄው ሆነ ማድረግ ያለብን እንዴት አድርገን ህጋዊ ሰላማዊና መዋቅራዊና መንግስታዊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሊስተናገድና ሊፈቱም ሆነ በቀጣይ በተሻለ ክባብልንታገልባቸው ወደሚችሉበት መድረክ እናሻግረው ነው። አለቀ።ካንተ የተሻለ አቅምም ሆነ ህጋዊነት ከሌለው አካል ይህን ስጠኝ አትስጠኝ። ተቀበል አትቀበል። ተው አልተወም ብለን አንጪቃጪቅ። አንድም እራስን ማሳነስ ነው። አልያም ባዶ ብራባዶ ነው። በዋናነትም ሁላችንምየሚጠየቀው ክፍልቢፈልግምበጭራሽ ሊፈፅመው የማይችለውመሆኑይግባን።

3.ፅንፈኛ፤ አቢዮታዊ፤ ግብታዊ ፤ ሰር ነቀል፤ ገንጣይ፤ ቅጂ የሆነ የመፍትሄ ሀሳቦች በሙሉ ተጨባጬንነባራዊ ሁኔታበጥልቀት ካለመረዳት፤ በይበልጥም ከተጣባ መጥፎ ልምድና ፖለቲካውን ወደኛ ፍላጎት ማዘንበል ይቻላል ከሚል የሚሰነዘሩ እብድ ሀሳቦች ናቸው።እነዚህን አይነት ሀሳቦች በጦዙበት ትብብር መፍጠር አይቻልም። ካልተባበርን ደግሞ ማሸነፍ የለም። ከታገልን ለማሸነፍ እንታገል።ወንዝ የማይሻገር የመፍትሄ ሀሳብ መወርወር እንጂ ተፈፃሚ ነው፤ ተቀባይስ፤ ጦሱስ የሚለውን አስፍተን እያየንአይደለም።ህዝብ ነፃነቱን አምርሮ በመጠየቁመራራ መስዋትንት እየከፈለ ነው።ለዚህ ሁሉ የሚያስተባብረው ቀላሉና ጭቅጭቅን የሚቀንሰውመንገድ ያለውን መነሻ ማድረግ ነው። ህገ መንግስቱ፤ ፌደራል ስርአቱ፤ መዋለንዋይ ድልድሉን ሆነ ውክልናን በተመለከተ ያለውን የስልጣን ድልድል በተጨማሪም አዲስ አበባንም በተመለከተ ካለው መነሳቱ የተሻለው ምርጫ ነው።

ያለው፤- ዲሞክራሲ፤ ነፃ ሜዲያ፤ ነፃ የፍትህ ስርአትና ነፃ ምርጫ በሌለበትና ጭቆና በነገሰበት ሁኔታ ውስጥ በዛ ላይበወረቀት ላይ የሰፈረው አንዱም ቁም ነገር ተፈፃሚ ባልሆነበት ለሀያ አምስት አመት ስራ ላይ የዋለ ነው። ተግባር ላይ እንደዋለይስራል አይሰራም ብሎ መከራከር ቢቻልም ትክክለኛ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አይደለም። አገዛዙ ይባስ ብሎ ያለውን ወዲያና ወዲህ እየዘወረ ስልጣን ላይ ለመቆየትና ተቀናቃኝ ያላቸውን ክፍሎች ሁሉ ለማሳደድ የተጠቀመበት ስለሆነ ተቀባይነቱ ላይ አስቸጋሪነቱ የሚጠበቅ ነው።ላንዳንዶች ማሰቡም ሊከብድ ይችላል።መታወቅ ያለበት ግን ያለው ወደፊትም ሆነ ወደኋላ ለመውሰድ የተመቸ አይደለም። ወደኋላ መሄድ የህዋልዬሽ መንገድ ይሆናል። ወደፊት ከተባል ወደገደል ሊሆን ይችላል። ወደኋላ በመንደርደር ጦሮ ሰብቆ በሚመጣም አካልሰላምሊፀና አይችልም። ከህዘብ ፍላጎት ውጪ ይሆናልና። ስለዚህ ይህምያው ገደል ውስጥ የሚከተንነው።

የተሻለው መንገድ ለሁላችንም ካለው መነሳት ነው።ሰፋ አድርጎ ለሚያይለሀያ አምስት አመት እንግዳ የሆነ አገዛዝ በነገሰበት እስከችግሮቹመሬት ላይ ባለውእንደ አንድ አገር ህዝብ መቀጠል ችለናል።ይጨመሩ ከሚባሉት የሙብት ጥያቄዎች በላይ በወረቀት ላይ የተቀመጠው ተፈፃሚ ይሁንልን የሚለው ድምፅ ነው መስዋትንት እየከፈለ ካለው ህዘብ ጎልቶ እየተሰማ ያለው።በዚህ ሀያ አምስት አመት ተፈጠሩ የምንላቸውን ችግሮች ነቅዘን እያወጣን አግባብ ያለው ህዝባዊ ውክልና፤ ዲሞክራሲ፤ ሙብትና ነፃ የዳኝነት ስርአት ተጨምሮበት ቢሆን ኖር በሚለው ውስጥ ብናሳልፋቸው አንዳቸውም ችግሮች ከመነሻውም አይፈጠሩም ነበር። ቢፈጠሩም አግባብነትና ህጋዊነት በጠበቀ በቀላሉ መፍትሄ ሊሰራላቸው የሚችሉነበሩ። አሁን በመሬት ላይ ያለውን ወያኔ ሙሉ በሙሉ ያስቀመጠውና ሙገሳ የሚያስገኝለትአይደለም። መፍትሄ በወረቀት ላይ ሰርቷል ቢባልም ለዚህን ያህል ጊዜ ስልጣን ተቆናጦ

ሊተገብረው አልቻለም። በዛ ላይ ለአገሩና ለህዘብ ድህንነት የምር ለሚቆረቆር መፍትሄውን ማን ሰራው ሳይሆን ይጠቅማል? ልንጠቀምበት እንችላለን? ሊያሻግረን ይችላል? የሚለውን ማየቱ ነው ትክክለኛው።

ከዚህ በፊት አዲስ ህገ መንግሰት ለሽግግሩ አያስፈልግም ሲባል ሁሉም ያስፈልጋል አለ። መቅረፁም ብዙ ስራ ነው።እንዴትና መቼሊፀደቅ የሚለው ስሌት ውስጥ ሳይገባ ስለነበር ሀሳቡ የሚገፋው የተሳሳተ ሆኗል። አሁን ከሽግግሩ በኋላ የሚለው ሃሳብ አስማሚ ይመስላል።አዲስ ሳይሆን በረጅም አመታት ውስጥ ቀስ በቀስበማሻሻል የሚለውም አማራጭ ሊሆን ይችላል።በአጠቃላይ ያለውን ለሀያ አምስት አመት ተግባር እንደዋለ ሳይሆንእንደ አዲስ በፅንሰ አሳብ ደረጃ ወስደን መነሳቱ ነው ለሽግግሩ ጊዜየተሻለ ነው። አንጃ ክራንጃ ባልበዘበት ሊያሻግረና አስማምቶ ሊያስተባብረን የሚችል ነው። ከተባበርን እናሸንፋለን ተጭቆናና አስቀያሚ ከሆነው አድሎ እንገላገላለን።

አሁን ያለው የያዛቸው አሰፈሪም አላስፈላጊም የማያስማሙ አንድና ሁለት የግድ መሻሻል ያለባቸው ጉዳዬች አሉ። እነዛን የሽግግሩ ቻርተር ላይ ማካተት ነው። በዋናነት በወረቀት ላይ ያለው በሙሉ በተገቢው ተፈፃሚ መሆን መቻሉን እናረጋግጥ። በተረፈ ነገ ቀጣይ ትውልድና መታገል የሌለ ይመስል ድርቶ አናብዛ። ይህን በማድረግ በቀላሉ መስማማት ይቻላል። በቀናነት ስለእውነት ካየነው እንናገር ከተባለ ያለው በአግባቡ ተግባር ላይ ውሎ ቢሆን ዛሬ ላይ በተቃዋሚነት ለብሄርና ብሄረሰብ መብት ብቻውንተነጥሎ የሚቆም ባልነበረ። ይህን የማነሳው ያአገሪቷ ሉአላዊነትና የአንድ አገር ዜጎች የመሆናችን ጉዳይ የምር ከሚያሳስባቸውና ለሁሉ ነገር መነሻ መሆን አለበት ከሚሉት ዜጎችና ክፍሎች ስለመታባበርና ስለሰላም ሲሉ አሁን ካለው ላይ ጨምረው እሺ ይሁን ሊሉት የሚችሉት ነገር የለም የሚለውን ለማሳየት ነው። ይህን ስል በጥሬው ነው። በአንዳንዶች በዚህ ፍላጎት ውስጥ የታጨቀ ሌላ ፍላጎትና ለወንድሞቻቸው መብትና ፍላጎት ላይ ንፉግነት፤ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ዜጎች ላይ ያለ አመኔታ፤ አልፎም መፍራት አንዳንዴም ጥላቻእንዳለ አውቃለው። አነሳሴ ሰከን ባለና ብልጠት ባለበት መራመድ በሚገባን ጊዜ ላይ መንቦጫራቅና መበሻሸቅ ስላየው ተንቦጫርቄ ማለዘብ ከተቻለ በሚል ነበር። የተደጋገመ ቢሆንም የምር ወደሆነው ሳልፈልግ ብዙ ተስቤያለው። ወደሰሞንኛው በቀጥታ ልግባ።

“በተበታተነች ኢትዮጵያ ውስጥ ካልሆነ የኦሮሞ ህዝብ ጥቅም ማስጠበቅ ስለማይቻል የምትበታተን እንጂ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የሚባል ነገር የለም”። ሊበን ዋቆ የድርጅቱን አቋም። የለንድን የኦሮሞ ህዘብ ኮንፈረንስ ላይ።

ብሄረሰብ የሚባል ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሌለ የብሄረሰብ ጭቆና የለም። ያለተበረዘው የኦሮሞ ህዘብ ቁጥር ከሰባት ሚሊዮን አይበልጥም”። ደ/ር ሀይሌ ላሪቦ ቀድመው ባስነበቡን ፅሁፍ ውስጥ።

“ሀይሌ ላሪቦ የኦሮሞ ህዘብ ቁጥር ከሰባት ሚሊዮን እንደማይበልጥ እቅጩን ነግረውናል። ሳይንሳዊ በሆነው መንግድ አይቼው ትክክለኛው የኦሮሞ ህዘብ ቁጥር ሰባት ሚሊዮ ሊበልጥ እንደማይችል አሳምኖኛል”። ዶ/ር ፍቃዱ በቀለ።

አምልክ በኢትዮጵያዊነት እንጂ በኦሮሞነት፤ በአፋርነት በጋንቤላነት አያውቃችሁም። ምክንያቱም ኦሮሞ፤ አፋር የሚባል ስም በመፃህፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። ፓስተር ቶለሳ ጉዲና ቀድሞ።

በዋናነት የፐ/ፌ መስፍን ወልደማርያም በቅርቡ ያቀረቡት መፍትሄ ሲጨመቅና መፃህፉቸውንና ከዛም በኋላ የኦሮሞ ህዘብ አመፅ ከጀመረ ጀምሮ የፃፏቸውን ፅሁፎች አጣምሮ ሊረዳ ለመኮረ እኔ እንደተረዳሁት ምን አልባትም ነገር የሚገባቸው ሌሎችም ሊረድት እንደሚችሉትከአማራ ክልል ወደትግራይ ያስገባችሁትን መሬት ብቻ መልሱና ከዛከባሰ የስልጣን ቅብብሎሽ እንጫወታለን ነው። ለኛ ለሰዎቹ ሲባል ለቀጠፍናቸው ቄጠማዎች ገንዘብ እንሰጣቸዋለን አይነት ነው።

ከላይ የተቀመጡት ሀሳቦች የበዙት ሊነበቡ፤ ሊታዩ፤ ሊደመጡ የሚገባቸው ተብለው የተገለፁ ነበሩ። እማኝ ተደረገዋልም። ለሀሳቡ አቅራቢዎች  ተራሩጦ  መድረክ ማዘጋጀት አለ። ሊበን ዋቂ ግን ተቀጥቅጧል። ሙብቱን የጠየቀ ህዘብ ላይ የአስቸኳይ ጊዜ በሚል እንዳገዛዙ በግልፅ አልተገለፀም እንጂ ዘመቻ የሚመስል ነግር ከጀመር ቆይቷል። ሊበን ዋቆ ቀድሞ ለጀመረ ዘመቻ ጭድ ነው ያቀበለው።በተጓዳኝ አገዛዙ ወቃሽ በሌለበት ህዝብ ላይ ዘምቷል። የሚችለውን ያህል እየገደለም እያሰረም ነው። ተመችቶታልም። ሊበን እንደገመትኩት የድሮ ካድሬ ነው። በየትኛውም አቅጣጫ ቢታይ ንግግሩ ላይ ትክክል የሆነ ነገር የለበትም። ባለጌም ነው። ብሽሽቁ ላይ የመልስ ምት ተደርጎ ሊታይ ይችላል። ነገር ግን ኦሮሞ እንደመሆኑ በሁን ጊዜ የበዛ ሀላፊነት ነበረበት። የህዝብን ትግል ልፊያ ውስጥ መክተትና የኦሮሞ ህዝብ ከወገኖቹ እገዛን እንዲነፈግመዶለት አልነበረበትም። ሌላው ሁሉ ቢቀር አቦይ ፀሀይዬ “ይተገበራል” “ልክ እናስገባለን” ብሎ  ለትግሉ ከጠቀመ እየተፈጀ ላለው ወገን ሲል እንኳ ሀላፊነት በተሞላበት ሊናገር በተገባ ነበር። ብቻ መቀጥቀጡ ሲያንሰው ነው። ሌሎች የተሞገሱት ትክክል ስለሆኑ ግን አይደለም። ማንን? የሚለው ነው እንጂ በእኩል የሚያናድድና ልፍያ ውስጥ እንድንገባ ያደረጉናቸው። ሰላሰፋው እያንዳንዱን በትንሽ መስመር።

ባለፈው ሀያ አምስት አመታት ውስጥ ኦሮሞ ነኝ ማለት በሚያስገድልበት፤ በሚያሳስርበት በሚያስገልልበት እውነታ ውስጥአንድ ሰው ሳይሆን ኦሮሞ ነኝ ለማለት ተሯርጦ እጅንአያወጣም። ከአገሪቷ ህዘብ ግን ግማሹ በቃ እኔ ኦሮሞ ነኝ ብሏል። ይህን ተራራ የሚያህል  እውነትና ዛሬን ሊያይ ያልቻለ ትናንት ላይ ተመራምሮ የታሪክ ምሁር  ቀልድ ነው። ስለዚህ ዶ/ር ሀይሌ ላሬቦ እራሱ አለ ወይ?።

አለምነው መኮንን ሲባሽር አማራ ሆኖ አማራን ሲሳደብ ባለጌ እንደነበረና ሙብት ተደርጎ እንዳልተወሰደለትፓስተር ቶለሳም ትክክል የሆነን ነገር የመናገር ግዴታ አለበት። ካልክ መፀሀፍ ቅዱስ ውስጥ  ዳዊት እንጂ ቶለሳ የሚል ስም የለምና አያውቅህም አታውቀውም ሊባል በተገባ ነበር። በእርግጥ ይህን ለማለት እንደምናመልከው አምላክ ነው።የብዙዎቻችን አምላክም እምነታችንም ቶለሳንም፤ ዳዊትንም በእኩልያውቋቸዋል።  በዛ ላይ ፓስተር ቶለሳ አገሪቷ ውስጥ ያለውን ግፍና በደል አላውቅም ሲል እውነትን አልተናገረም። እየተፈጀ ካለው ወገኑጉዳይ ሳይገደው ለቂስ ሲያለቅስ ሁላችንም ሰምተንዋል።

ምንም መሰረትም እውነታም ባይኖረው ብዙዋቻችን ዘረኝነትን ካለማወቅ ጋር ነው የምናገናኘው። መቼ የት ቦታ ላይ ነው ካለማወቅ ጋር የተቆራኘውቢባልመልስ ያለው አይመስለኝም። ዘረኝነት የተሻለ የሚዛመደው ከእውቀት፤ ከስልጣን፤ከመሳርያ፤ ከሀብት፤ ከተደማጭነት ብቻ ከሀይልጋር ነው። እኛ ሰዎች ነን። እኛ የተሻልን ሰዎች ነን የሚለውን የሚያመጣውም ይህው ነው። ጊጂም የሚሆነው ያኔ ነው። አንድ ሰው ስለአንድ አገርናህዘብና አገር እያወራ ለኛ ለሰዎቹ እያለ ቢቀኝም ምን ለማለት እንደተፈለገ ገብቶናል ፅድት ያለ ንቀትና ጥላቻን እያራመደ ነው። ስህተትም ነው። አይጠቅምም። እኔ ነፃ ኦሮሚያን የማያት ሊበን ዋቆ ጭንቅልት ውስጥ ሳይሆን ፐ/ፌ መስፍን ወለደማርያም ጭንቅላት ውስጥ ነው።

ሳይንሳዊ እንጂ ምክንያታዊ አይደለም መሆን ያለብን ከሚለው ክርክር ጀምሮ ሁሉም ፅሁፎቾት ላይ ሳይንስ የገባበት ቦታ ስደርስ ሁለት ሶስቴ ተመላልሼ አነብ ነበር። ሳይንስ ሆኖ ስላልገባኝ ነበር የእስካሁን ግምቴ። አሁን ግን አልመሰለኝም። ዶ/ር ፍቃደ በቀለ ነኝ ብለውአራሶትን ይገልፃሉ።ለዚህ የሚሰጡትን ሳይንሳዊ ትንታኔ እኔ ኦሮሞ ነኝ ለሚል ግለሰብ የማይሰራበትን የሚለይበትን መንገድ ሳይንሳዊ በሚሉትመንገድ ሊያሳዩት አይችሉም። "እንደ ኢትዮጵያዊ እንጂ እነደ ኦሮሞ ማሰብ ሳይንሳዊ አይደልም"። "የገዳ ስርአት የከብት አርቢዎችና የዘላኖች የሆነ ለእድገትና ለሳይንስ የማይሆን ስርአት ነው"። እነዚህ የመሳሰሉ ትንታኔዎች አንድን ሰው ሳይንሳዊ አይደለም ባህላዊስ አዋቂ ሰው እንዴት ያደርጉታል። በሳይንስ ለመደብደብ በመጀመርያ ሳይንሳዊ መሆን አያስፈልግም ወይ?። ሌላው ቢቀር እዚህ የቆየ ስርአት ውስጥ ያሉ ብዙዎቹ እሴቶች ይህው እስከ ሀያአንደኛው ዘመን ብንመኘውም ልናመጣው ሆነ ልንተገብረው ያልቻለነው ነው። የሰለጠነው ማህበረሰብ ግን የሚጠቀምባቸው ናቸው።በዋናነት ሰዎች ያስቀመጡት ስርአት ነው። አሁንም ሰዎች ቁጭ ብለው ማሻሻል አይደለም ለሌላ 21 ክፍለ ዘመን ደግሞ የሚሻል አድርገው ሊሰሩት ይችላሉ። አሁን ባለበትም እስካሁን ካልን ግን በእጅጉ የላቀ መሆኑ እውነት ነው።

የቢሾፍቱ ፍጅት ተደማጭነት ከለከለው እንጂ ከሊበን ዋቆ በፊት ዳዊት ኢብሳ በትእዛዝተናግሯል። ሰምቼው ንግግሩ ጎጂ እንደሆነ አውቄፈርቼም ተናድጄም ነበር። ለምን እንደው አላውቅም ትግሉ አለቆ ከስልጣን የተገፋ አይነት ብቻ ነብስ ይማርና እ/ር ሀይሉ ሻወልን አስታውሶኛል። ሊበንም ዳውድም የተናገሩትን የተናገሩት በዋናነት ለኛ አልነበረም። ያነጣጠረው ሌላ ቦታ ነው። ትግሉ ላይ አንጋፋ ከሆንክ ስራ ካልሰራህና አስተዋፆ ከሌለህ የተረሰህ ስለሚመስልህ ቀላሉ መንገድ እኛ ከነሱ የተሻልን ኢትዮጵያዊያን ነን እንደሚሉት አይነት እኛ የተሻልን ኦሮሞ ነን ነው ጉዳዩ። እነሱ ግን?.......አይነት ነበር መልእክቱ የነበረው። መረሳት፤ አለመፈለግ፤ እኛም አለን፤ ለፍተን ለፍተን… የተራዘመ ትግል የሚያመጣው የዚህ አይነት ውስብስብ የሆነ የአስተሳሰብ አይነቶችስለሚኖርሀላፊነት ተስምቷቸውለባለተራዎች ትግሉን ይመሩ ዘንድ መተው አቅቷቸዋል።የዚህ አደገኛነቱትግሉ ላይ እንዳየነው ሳንካ መሆን ብቻ አይደለም።ጭቆናው ቢቀጥል ይሻላልን ምርጫቸው ሊያደርጉ ሁሉ ይችላሉ። እነዚህን ጥሎ መሄድም እንደማይቻል ወይ ቀላል እንዳልሆነ በቅንጅት ጊዜ አይቼዋለው። ትግሉ ቢተውላቸውም ደግሞመቼም ታግለው አያሸንፉም።ሁላችንንም ተሸናፊ አድርገው ይሞታሉ። እጅግ የከበደ ቀላል መፍትሄ የሌለው ችግር ነው።

ውስጥ አዋቂ አይደለሁም። ከርቀት ሆኜ እንደምረዳው የኦሮሞወች ጉባኤ አነሳሱ አስፈላጊም፤ ጠቃሚም፤ ለመልካም አላማም የታሰበ ነበር። ነገር ግን ይህ አይነት ጥረት ይሳካ ዘንድ የታደሙት ሁሉ እኔና እኝ የሚለው ፍላጎትን ማሸነፍን ይፈልግባቸው ነበር። በይበልጥም የምንታገለውን አካል ባህሪ በማወቅ ፍጅትን ማስቆም ቅድሚያ መሆን ነበረበት። ዋና አላማ መሆን የነበረበት ትግሉን መሰዋትነት በቀነሰበት ባጭር ጊዜ ባለድል ማድረግ ነበር። ይህ ይሆን ዘንድ በኦሮሞዎች ዘንድ ጠንካራ ህብረትን ከመፍጠር በዘለለ ትግሉን አገራቀፋዊ መልክ ማስያዝ አስፈላጊ ነበር። እውነታው የኦሮሞ ህዝብን አንድነት ትግሉ ሰርቶታል። ስለዚህም ጉባኤው ታሳክቷል ቢባልም በታለመለት መሰረት ስኬታማ አልሆነም የሚል ነው ግንዛቤዬ። ለዚህ ማን ተጠያቂ እንደሆነ ደግሞ ግልፅ ነው።

የሰው ልጅ ትልቁ ጉልበት ጭንቅላቱ ነው። ማንም እዚህ ትግል ላይ አስተወፆ የምር ማድረግ የሚፈልግ ከሆነ ተቀበሉትም አልተቀበሉት በጭንቅላቱ ያድርግ። የኛ ትግል የጎደለውም አሸናፊም የማይሆነው ጭንቅላት ስለሚጎድለው ነው ብዬ ከደመደምኩ ቆይቻለው። የኦሮሞ ህዝብ አቢዮት በአገር ደረጃ ትግሉ ላይ በግማሽ የሰው ጭንቅላትሲንንቀሳቀስ እንደነበርአሳይቶኛል። ትግሉን ከትብያ አንስተው አሁን ያለበት ደረጃ አድርሰውታል። በየቀኑ አዳዲስ አዋቂዎችን ሲጎርፉ አይቼ

ተደምሚያለው። እነዚህን ቄሮዎች በአማርኛ የሚናገሩትን አይደለም በኦሮሚኛ የሚናገሩት ቋንቃውን ባይሰሙም በጉጉት ጠብቀው የሚያዳምጡ ብዙዎች ገጥመውኛል።

ከጥቂት መሪዎቻችን በቀር ባህል የሆነውትግሉንም እንመራለን ፖለቲካውንም እናካሂዳለን የሚሉት ከቁም ሳጥን ጀርባ ተደብቀው ነው። ደፍረው እራሳቸውን ለህዘብ ቅርብ ያደረጉት በመጨረሻ የተሻሉ ሆነው ቢወጡም ተቀጥቅጠውና አንዱን ሲያልፉት በሌላ ሾኬ እየተዳፉ ነው። ሰርጎ ገብ ወያኔዎች ነበሩ፤ ሲአኤዎች ነበሩ። ከወያኔ ጋር ተሞዳሚጆች ነበሩ፤ ለምን ብሎ መጠየቅ አይጠቅምም አገርን ወይ ይህን ወይ ያን ማህበረሰብ ክፍል ለመጉዳት ነው አላማቸው.....በዚሁ አይነት ሁኔታ አሁንም ማደናቀፉ ቀጥሏል። ቄሮዎች ለአንድ አመት ሌሎቹ በሙሉ ባንድ ላይ ለህዝብ እራሳቸውን ከገለጡት በላይ እራሳቸውን ገልጠዋል።ለህዝብ በዚህ ደረጃ ቅርብ ስትሆን ለመሳሳት ትክክልም ሆነህ ይህን ወይ ያን ወገን የማስቀየም እድልህ የበዛ ነው። ጥያቄው ይጎርፋል። አንዳንዴ እየተዶለተመሆኑንም አንርሳ። አስቸጋሪ በሆነ የፖለቲካ ባህል እጅግ በተከፋፈለ ማህበረሰብ ውስጥ እንደሚሰሩ ግምት ውስጥ እናስገባ። ሰው ሲናገርና ፅፎ የሚሳሳተውን በእኩል አንመዝን። ሲሳቱ እያረምናቸው ለኛ ቅርብ መሆናቸውን እንውደደው።

ብሔራዊ ጭቆና ይብቃ።